«መቅደላ»የአንድነት ራዕይ ባለቤት
የሆኑት መሪዎችን ግርማ
ሞገሥ በተላበሰ ጀግንነት
የሸኘች፣ራዕዩን ለተከታዩ
ትውልድ ያስረከበች የታሪክ
ቦታ በመሆኗ ታሪካዊ
ፋይዳዋን ለመዘከር
የልሣናችን መጠሪያ
እንድሆን መርጠን!

# መቅደላ

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን
ቃል ኪዳን ነው!

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት
እንታደግ!

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ
አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)

Amara Survival for Ethiopia's
Unity Organization (ASEUO)

## የሀኅኢአድ ማዕከላዊ ምክር ቤት ልሣን

### የዐማራው ኅልውና መጠበቅ፤ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ቅጽ** 01 | **ቁጥር** 001 | ቀን፦ ኅዳር 6/2010 | ዘወትር ኅሙስ ኅሙስ በ15ቱ ቀን የሚወጣ |

## ከትግራይ ሕዝብ ዝምታ ጀርባ፣

በቅርቡ የወያኔ የወግ ዕቃ የሆነው፣ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃይለማርያም ደሣለኝ በሰጠው መግለጫ፣ የኦሮሞና የዐማራ ሕዝብ የፈጠሩትን አንድነትና ያሳዩትን ወንድማማችነት፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በዐማራውና በትግራይ ሕዝብ መካከል እንደሚካሄድ ተናግሯል። በእርግጥ፣ የትግራይ ሕዝብ በረጅም ጊዜ ታሪኩ፣ከአጎራባቹ የዐማራ ነገድ ጋር በፍቅርና በመተሳሰብ ተደጋግፎ ከመኖሩ በተጓዳኝ፣ የተጋባና የተዋለደ፣ ክርስትና ፣ እስልምና እና ይሁዲ ሃይማኖቶችን ተጋርቶ የኖረ ወድማማችና እህትማማች ሕዝብ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም የተነሳ፣ ለትግራይ ሕዝብ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎና ሸዋ ክፍለ-ሀገሮች ቤታቸው፣ መኖሪያቸው፣ የወግ ማዕረግ ማያቸው እንደሆነ በየታላላቅ ከተሞች የሚገኙት ሆቴሎች፣ ጋራጆች፣ ሱቆች፣ ሠፋፊ እርሻዎች፣ የቤትና ቢሮ ዕቃዎች መለስተኛ ፋብሪካዎች፣ ወዘተ ባለቤቶች የነማን እንደሆኑ የምናውቀው ነው።

በታሪካችን ለሥልጣን ሲባል ከሚደረግ የሥልጣን ተሻሚዎች ፍትጊያ ውጭ፣ በረጅሙ ታሪካችን፣የዐማራና የትግራይ ሕዝብ ግንኙነት የሰምና የፈትል፣ የወተትና የውኃ ያህል ለመለየት የማይቻል፣ በልዩ ልዩ መንገዶች የተያያዘና ውሕድ አካል እንደነበር ይታወቃል። ይህን የቆየና መልካም ትስስርና ዝምድና ግን፣ከትግራይ ሕዝብ አብራክ ወጣን የሚሉን ወያኔዎች፣ ከዐማራው ላይ በተለይም በጎንደሬው ላይ የሚያሳዩት ደመኝነትና ዘር እስከ ማጥፋት የደረሰ ጥላቻ ከምን የመነጨ ነው? ብለን እንድንጠይቅ አስገድዶናል። ለጥያቄው የተለያዩ መልሶች መስጠት የሚቻል እንደሆነ ብንገነዘብም፣ ለዐማራው ጥያቄው እንቆቅልሽ ሆኖበት ለ26 ዓመታት በዝምታና በትዕግሥት ሲመለከት ቆይቷል። ነገሩን የበለጠ አጠያያቂ የሚያደርገው፣ ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ በውድም በግድም ዐማራውን በጠላትነት እንዲመለከተው ከማድረጋቸው በተጓዳኝ ፣በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ነገዶችን «ዐማራው የእኛም የእናንተም የጋራ ጠላት ነው፤ እርሱን ለማጥፋት ተባበሩን» ማለታቸውና በመላ አገሪቱ በሚኖረው ዐማራ ላይ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንዲፈጸምበት ጃዝ ! በለው! ብለው ዘመቻ መክፈታቸው ነው። ዐማራው በጥቅሉ ትግሬንም ሆነ ሌሎች ነገዶች ላይ ምን በደለ ፈጸመ?

የአንድነት ኃይሉ በተለያዩ ምክንያቶች ተበታትኖና ተዳክሞ፣ ተገንጣዩቹና ብሔርተኞቹ በለስ ቀንቶአቸው ወደ ኢትዮጵያ ማዕከላዊ የፖለቲካ ሥልጣን አናት ላይ ሲወጡ፣ ዐማራው ማለትም ሸዌው፣ ጎንደሬው፣ ጎጃሜውና ወሎየው እንደ ነገድ፣ ወይም እንደ ክፍለሀገር በማሰብ ለምንና እንዴት ብሎ የተለየ ቅሬታ የገለጸበት ሁኔታ የለም። ከሁሉም በላይ ጎንደሬውና ወሎየው ለም የአባቶቹን አገር ወልቃይት፣ ጠገዴን፣ ጠለምት፣ ሡቲትንና ራያና አዘቦን ሲነጥቁት፣ የነዚህን ወረዳዎችና አውራጃ ተወላጆች ተገድለውበት፣ አሰቃይተውበትና አሰድደውበት እያለ፣ያሳያቸው የጥላቻም ሆነ የተቃውሞ ድምፅ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልነበረም።

የተቃውሞ ድምፅ ፈጥኖ ያላነሳውም፣ በጎንደሬና በትግሬ፣በትግሬና በወሎየ መካከል የነበረውን ጥንታዊ ዝምድናና ጉርብትና ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ «አድሮ እንየው፣ ሲረጋጉ ሁሉም ወደ ነበረበት ይመለሳል፤ እንደ መንግሥት ሲያስቡ ይስተካከላል» በሚል እሳቤ፣ ለም መሬቶቹን ተነጥቆ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈጽምበት«ጊዜ ያመጣውን ጊዜ ይመልሰዋል» ብሎ ትዕግሥትንና ዝምታን መምረጡ ግልጽ ነው። ይህን ወያኔዎቹ ያጡታል አንልም። ይህን ግን እንደፍራት በመቁጠር «ጠብ ያለሽ በዳቦ፣ ዓይነት የሆነና የላም አሸናፊ በሚመስል መልኩ ዐማራውን አሳደህ በለው ለምን አስፈለ?

በየክፍለሀገሩ ተወስኖ የሚኖረው ጎንደሬም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች የሚገኘው ዐማራ ላይ የሚደርሰው በደል ሳያንስ፣ በኢትዮጵያ ምድር፣ አያት ቅድመ አያቶቹ ደማቸውን አፍሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ባስጠበቋት አገር፣ አገሬ፣ ወገኔ ብሎ ተዋልዶና ተሳስቦ የሚኖረውን ዐማራ እያሳደዱ ማጥቃት፣ ማፈናቀልና ማሰር፣ አገርህ አይደለም ውጣ ማለት ለወደፊቱ አብሮ የሚያኗኑር ነው ማለት ይቻላል ወይ?

አምላክ፣ እስካሁን ዐማራው ያየውን መከራ ተመልክቶ፣ የትግሬ-ወያኔ ባቀበላቸው ዱላ ይደበድቡን የነበሩትንና እንደአውራ ጠላት ያዩት የኦሮሞ ብሔርተኞች ጎንደር ላይ «የኦሮሞ ደም ደማችን ነው!» ብሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያሰማ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በበኩሉ «የጎንደር ደም ደማችን ነው!» ቀጥሎም «ጣና የእኛ ነው» እያሉ ድምፃቸውን ማሰማታቸው፣ዐማራው ሊያመረቅዝ ያለውን ቁስሉን የማጥገገ ምልክት እንዲያሳይ በማድረጋቸው፣ድሮም ቢሆን ልዩነት ያልነበራቸውን የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች ድርጊቱን ዐማራው በደስታ ተቀብሎ ማስተናገዱን እያስተዋል ነው።

ይህ የኦሮሞዎች ቀና አመለካከት በእርግጥ የዐማራ ወንድምና እህቶቹን ልብ ነክቶታል። ወያኔ በኦሮሞዎቹም ላይ እንደ ዐማራው ሁሉ ተደጋጋሚ ግፍ የፈጸመባቸው በመሆኑ፣ ከኢትዮጵያዊነታችን ስሜት በላይ፣ በጋራ የደረሰብን በደል ተመሳሳይ በመሆኑ፣ የዐማራው ደም ደማችን ነው ያሉትን ጥሪ የተቀበልነው በአዎንታዊ ጎኑ ነው። በሌላ በኩል ይህን የኦሮሞዎችና የዐማራዎች ወደ ነበረበት ወደ ጥንቱ የአንድነትና የአብሮነት ትስስር ለመመለስ የተጀመረውን መልካም ጅማሮ ለማደናቀፍና የልጆች ጨዋታ ለማድረግ ተመሳሳይ ወያኔአዊ ደባ በትግራይ በኩል ስንሰማና ስናይ፣ ወያኔ የሚሰንቀው የጥፋትና የከፋፍለህ ግዛው ቅያስ እስከ መቼ? ብለን ጥያቄ እንድናነሳ ተገደናል።

በተደጋጋሚ ለማሰማት እንደሞከርነው፣ የዐማራው ነገድ ከትግራይ ነገድ ጋር ጠብ የለውም። ጠቡ ያለው የትግራይ ሕዝብ የአብራክ ክፍያ ከሆነው ወያኔና አስተሳሰቡ ጋር ነው። ይህም በመሆኑ የትግራይ ሕዝብ ወያኔን ወክሎ ከጎንደር ሕዝብ ጋር እርቅና ሰላም ለማውረድ ወደ ጎንደር የሚመጣበት ምክንያት የለም። ምክንያቱም ሕዝቡ እንደ ሕዝብ ጠብ የለውም። ጠቡ ያለው ከወያኔና ከሥርዓቱ ጋር ነው። ይህ ደግሞ የዐማራም የትግሬውም ጠላት ነው። ስለሆነም ሽምግልና ከሆነ ሽምጋዪ ወያኔ የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን ሳይሆን፣ ከሁለቱም ወገን ገለልተኛ የሆኑ፣ በሁለቱም ነገዶች ከበሬታና ይሁንታን ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህ ሳይሆን፣ በወያኔ የሚመሩና አድርጉ የተባሉትን የሚያደርጉ ትግሬዎች ወደ ጎንደር የሚሄዱ ከሆነ፣ ነገሩ«በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት» ይሆናል።

ከትግራይ ሕዝብ መካከል፣ለሽምግልና ይበቃል የሚባል ካለ፣በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ወያኔ ከሥልጣኑ ገለል እንዲል መጠየቅ ብልኅነትና አዋቂነት ነው እንላለን። ይህን አደረጉ ማለት በወያኔ አረመኔአዊ ሥራዎች የተማረረው ወጣት በትግራይ ሕዝብ ላይ የቋጠረውን ቂም ወደ ብቀላ እንዳያሸጋግረው የሽምግላና ሥራ ሠሩ ማለት በመሆኑ፣ በታሪክ የትግራይ ሕዝብ በአገር ሻጭ ልጆቹ የጎደፈ ስሙና ዝናውን ለማደስ ቻለ ማለት ነው።

የዐማራውም ሆነ የኦሮሞው ጥያቄ «የወያኔ በዘረኝነት ላይ ያተኮረ የበላይነት ይወገድ ነው»፤ የትግራይ ሕዝብ ላለፉት 26 ዓመታት ወያኔ በኢትዮጵያውያን ላይ፣ ከሁሉም በላይ ዐማራው በደመኛ ጠላትነት ተፈርጆ የዘር ጥቃት ሲፈጸምበት፣ አንድም ድምፅ ያላሰማ፣ ዛሬ ወያኔ ከሥልጣን እንዲወገድ የተጠናከረ ድምፅ ከሕዝቡ ሲሰማ፣ ያን ለማደናቀፍ የሕዝቡ ጣልቃ ገብነት፣ ከምን መነጨ? ብለን እንድንጠይቅ አስገድዶናል። ይህ የትግራይ ሕዝብ ጣልቃ ገብነት፣ ሕዝቡ በዘረኛው አገዛዝ ላይ የሚያደርገውን ትግል፣ለማደናቀፍ ካልሆነ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል አይደለም። ከትግራይ በኩል የወያኔን ዕድሜ ለማራዘም የሚደረግ ሙከራ፣ጠቡን፣ ሲሠፋ በትግራይ ሕዝብና በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ሲጠብ ከዐማራውና ከኦሮሞው ሕዝብ መካከል እንዲሆን መጋበዝ ነው። ስለሆነም የትግራይ ሕዝብ ዘንባባ ይዞ ወደ ጎንደር ሊሄድ የሚያስችለው ሁኔታ ሊኖር ፈጽሞ የለም። በወያኔ አገዛዝ ሕዝባችን የቂም ቁርሾ አርግዟል። ይህ ጥላቻና ቂም ከኢትዮጵያ ሕዝብ አዕምሮ ሊወገድ የሚችለውና ሰላም የሚወርደው፣ ወያኔ ተወግዶ፣ በአገሪቱ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ሲሰፍን ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት። አይደለችም ብለው ጥለዋት ለመሸሽ ወይም ለመገንጠል የሚመኙና የሚሞክሩም ካሉ፣ሌላው ራሱን መሸከም የማይችል አንገት የለውማና የመጣውን እንደአመጣጡ ለመቀበልና ለማስተናገድ ይቸገራል ተብሎ አይታሰብም። በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ፣የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር፣ወያኔ ከሥልጣን ሳያስወግድ ይበርዳል አይባልም። ይህ ነባራዊ ሁኔታው የሚያሳየን ዕውነታ ነው። ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ፣ የጊዜ መግዣ እርምጃ ሕዝቡን ሊሸነግል የሚያደርገው ሸር ጉድ የትም ያደርሰዋል አይባልም።

ወያኔ ወጥሮ የያዘውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ግለት ለማብረድ፣ «ኦሮሞዎቹ» የሚፈልጉት የእኛን (ወያኔን) መውረድ ሳይሆን፣ ሥልጣን ለእኛ ይገባል» የሚል ነው በማለት የኦሮሞውን እንቅስቃሴ፣ በአፋዊ ሥልጣን ስም ለመሸምገል ዝግጅት እያደረጉ እንደሆነ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሠረት፤ ለማ መገርሳን ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ግርማ ብሩን አፈጉባኤ ለማድረግ ማጨታቸው ይሰላም። ለዚህም ለማ መገርሳ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ኢትዮጵያዊነትን እንዲሰብክ፣ እነርሱ ሆን ብለው -እሳትና ጭድ አደረግነው» ያሉትን ኦሮሞና ዐማራ ሰላም አሰፈን ለማለት፣ ለማ መገርሳ በርካታ ኦሮሞዎችን አስከትሎ ባሕዳር ከብአዴን አመራር ጋር መነጋገሩና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተከፍቷል። ወያኔዎቹ የቱን ያህል ሰውን እንደናቁ በሚያሳይ መልኩ፣ ኦሮሞዎቹ አፋዊ ሥልጣን ካገኙ የወያኔን ጥቅምና የበላይነት አይቃወሙ የሚሉ ወሬዎችን እያራገቡ ይገኛሉ።

ኦሮሞዎቹ ከዲሞክራሲያዊ ምርጫ ውጪ፣ ወያኔዎች እንደሚሉት በተሰጣቸው አፋዊ ሥልጣን ተደልለው የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ ወደ ጎን የሚሉ ከሆነ፣ ኦሕዴድ  እና ተከታዮቹ ዕውነተኛ የወያኔ እጀታዎች (ዛቦች) መሆናቸው ይፋ ይሆናል። የኦሮሞ ሕዝብም በነርሱ እንዳፈረ ይኖራል። ኦህዴድ ይህ ንቀት የተሞላበት የወያኔ አስተያየት ቁጭት ውስጥ ካልከተታቸው፣ ምን ሊከታቸው እንደሚችል የሚያውቁት እነርሱ ብቻ ናቸው። ስለሆነም የኦሕዴድ አመራርና አባላት የታሪክ ተጠያቂ የሚያደርገውን ሳይሆን፣ የታሪክ አንፀባራቂ ኮከብ የሚያደርገውን ሕዝባዊ ጎዳና እንደሚመርጡ ይጠበቃል። ተባብረን ወያኔን የምንጥልበት ወቅት ዛሬ ነውና፣ «ነጣጠልነው፣ እሳትና ጭድ አደረግነው፣ የወያኔ ኅልውና በዐማራና ኦሮሞ ፍቺ ላይ የተመሠረተ ነው» ያሉትንና ለመከፋፈል ብዙ ርቀት የተጓዙበትን መንገድ ተረድተን፣ የነርሱ መጥፊያ የሆነውን ፍቱን መፍትሄ የዐማራና የኦሮሞ ሕዝብን ወደ ነበረበት አንድነት የመመለሱን ጥረት በተከታታይ አጥብቀን በመሥራት ወያኔ የፈራው ዕውን እንዲሆን ማድረግ ይጠብቅብናል።

ዐማራና ኦሮው ብቻ ሳይሆን፣ መላው የአገራችን ሕዝብ አንድነታችን አጽንተን አብረን መኖር የምንችለው ከሥልጣን ጋር የተያያዘውን ብልጣብልጥ መንገድ ትተን ቀናና ሕዝባዊ የሆነውን ጎዳና ስንከተል ብቻ ነው። ወያኔ ማጣፊያው አጥሮበት የሚጨብጠውና የሚለቀውን አጥቷል። በመሆኑም «የሞኝ ዘፈን ሁልጊ አበባዬ» እንዲሉ ፣ ወያኔ ሕዝባችን ከመለያየትና እርስ በርስ እያናከሰ የአገዛዝ ዕድሜውን ከማራዘም ውጭ፣ የተለየ ነገር ይፈጥራል ብሎ ማሳብ የዋኅነት ነው።  እናም ለ26 ዓመታት በዝምታው የሚታወቀው የትግራይ ሕዝብ ፣ ዛሬ ልናገር ካለ፣ በተለይም ወያኔ ሆን ብሎ የዘር ማጥፋት ወንጀል ከፈጸመበትና ለም መሬቱን ከተነጠቀው የጎንደር ሕዝብ ጋር «የበደለ ሳይክስ፣ የተበደለ ሳይካስ» በዕርቅና በሰላም ስም ዘንባባ ይዠ ጎንደር እገባለሁ ካለ፣ወያኔ እስከ ዛሬ ሲፈጽም በኖረው ግፍ ጀርባ ነበርኩ፣ ተባባሪ ነኝ፣ ብሎ የማመን ያህል ስለሆነ፣ይህን ያደርገዋል ብለን አናምንም። ካደረገም እዳው ገብስ ነው። ጠላታችን ለየ ማለት ነው። ችግር የሚሆነው ወያኔን ከሕዝቡ መለየት ስለነበር፣ አሁን ያን ሥራ አቃለለ ማለት ነው።

በወያኔ አድርጉት ባይነት፣ የትግራይ ሕዝብ ወኪሎች ነን ያሉ ወደ ጎንደር ከመጡ ፣ ያ አፋችን ሞልተን የምንናገርለትና የምንመሰክርለት፣ ትናንት በኢትዮጵያዊነቱ የምናውቀው ሕዝብ አይደለም ማለት ነው። ትውልዱ ተኮላሽቷል፣ ታሪካችንም ዋሽቷል ማለት ነው። እንግዲህ ወያኔ ከተመኘው ፣ እኛም ከምንፈራው መከራ ሁላችንም ሰውሮ፣ በአገራችን ሰላምና አንድነት የራቀው ሕዝባችን ሰላሙና አንድነቱ ተመልሶ የምናይበትን ቀን እንዲያቀርብልን የአምላካችን ፈቃዱ እንዲሆንልን እየተመኘን፣ ለትግራይ ሕዝብ ልቦና ይስጥልን እንላለን!

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላምና በፍቅር

ለዘላለም ይኑር!

Amara Survival for Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)
ዐኀኢአድ
ASEUO